# የመላው ኢትዮጵያውያን ተስፋ!

ክፍል ሁለትና የመጨረሻ

ከተስፋዬ ለማ

03/28/14

በክፍል አንድ የግብጽ ዲፕሎማሲ የተሳሳተ መርህና እውነታ ላይ ያልተመሠረተ በመሆኑ ምክንያት መክሸፉንና ምንም ዓይነት ውጤት የማያስገኝ መሆኑን ለማየት ተሞክሯል። ከዚሁ ጎን ለጎንም ጦርነት እንደ አማራጭ ትጠቀማለች የሚለው የግብጽና የወዳጆቿ ፕሮፖጋንዳ ሕልም ላይ የተመሠረተ እንጂ መሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ ከንቱ ምኞት እንደሆነ ተነስቷል። በዚህ ሁለተኛና የመጨረሻ ክፍል ደግሞ የኢትዮጵያ የውስጥ አቅም ማደግ፣ የህዝቧ ተነሳሽነትና የግብጽ ብቸኛ አማራጭን እናያለን።

እነዚህ ወገኖች በመጀመሪያ ኢትዮጵያውያን የውስጥ አቅም ስለሌላቸው በዓባይ እንደዚህ ዓይነት ግዙፍ ልማት ሊገነቡ አይችሉም የሚል አቋም ነበራቸው። ታላቁ የህዳሴ ግድብን የሚያክል የልማት ፕሮጀክት ለመገንባት ከዓለም ማኅበረሰብ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማግኘት አለባቸው የሚል እምነት ይዘው ነበር።

በዚህ ምክንያት የመጀመሪያ ጥረታቸው አበዳሪ አገራትንና ተቋማትን እየፈለጉ ለኢትዮጵያ ድጋፍ እንዳይሰጡ ማድረግ ነበር። ይህንን ለማድረግ ሰፊ ዘመቻ በቀጣይነት አደረጉ። በሚያጋጥመው የፋይናንስና የቴክኒክ ችግር ምክንያት ግድቡ እንዳይሳካ ለማድረግ ያለ የሌለ አቅማቸውን አሟጠው ሰርተዋል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ቀድሞውንም ቢሆን ፕሮጀክቱን የነደፉትና ወደ ሥራ የገቡት የውጭ አገራት የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍን በማሳብ አልነበረም። ሁሉም ነገር በኢትዮጵያውያን ብቻ ለመሥራት ተዘጋጅተው ነበር ወደ ሥራ የተገባው። በውጭ የሚኖሩም ሆነ አገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለግንባታው መሳካት የድርሻቸውን እየተወጡ ግንባታው በታቀደው መሠረት እየተከናወነ ይገኛል።

ይልቁንም የውጭ ጠላቶች በበዙ ጊዜ በቁጭት በመነሳሳታቸው ለግድቡ መሳካት ያላሳለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። በዚህ ምክንያት ልማቱ በተገቢው መልክ እየተከናወነ ይገኛል።

ይህ የሚያሳየው አገሪቱ ሌሎች በሚያስቡትና በጠበቁት የእድገት ደረጃ ላይ አለመሆኗን ነው። ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በርካታ አኩሪ ለውጦችን አስመዝግባለች። ከእነዚህ በዋናነት የሚጠቀሰው በአገሪቱ የትምህርት ዘርፍ መስፋፋትና መጠናከር ነው።

ዜጎች በአገር ውስጥ በተስፋፋው የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ በመሆን በተለያየ ዘርፍ በቂ ባለሙያ ሆነው የሚወጡ ወጣቶች ቁጥር ከዓመት ዓመት እያደገ መጥቷል። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ የውጭ አገራት ሂደው ለሚመሩ ወጣቶች ዕድሉ ክፍት ተደርጓል። ማንኛውም ዜጋ በፈለገው አገር ሂዶ የመማር መብቱ ተጠብቆለታል። በዚህ ምክንያት በአገሪቱ አጠቃላይ የሰው ኃይል ልማት ቀላል የማይባል ለውጥ መጥቷል።

ከድህነት ተላቀው በከፍተኛና መካከለኛ ባለሃብትነት እየተመዘገቡ ያሉ ዜጎቿ ቁጥርም ቀላል አይደለም። በከተማ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ባለሃብቶች ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ኢንቨስተርነት መሸጋገር ችለዋል።

በገጠርም ከዚህ በላቀ መልኩ አርሶ አደሩ የዕለት ተለት ህይወቱን ከማሻሻል አልፎ ወደ ኢንቨስተርነት መቀየር ተጀምሯል። ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ከአርሶ አደርነት ወደ ከፍተኛ ኢንቨስተርነት የተሸጋገሩ አርሶ አደሮች ቁጥር ቀላል አይደለም።

በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አርሶ አደሮች ከአርሶ አደርነት ወደ አንደኛ ደረጃ ኢንቨስተርነት መድረሳቸው በአገሪቱ ያለው አጠቃላይ ለውጥ ያመላክታል። የአገሪቱ አጠቃላይ የምጣኔ ሀብት እድገት በአገሪቱ እየፈራ ካለው

በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ጋር ተዳምሮ የህዳሴውን ግድብ ዳር ለማድረስ ለኢትዮጵያውያኑ የሚቸግር ሆኖ አላገኙትም።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ወቅቱን ጠብቆ እየተገነባ ያለው አገሪቱ የምጣኔ ሀብት አቅሟን ማሳደግ በመቻሏ ነው። የዚህ ግንባታ መጠናቀቅ ደግሞ የበለጠ ወደ መከካለኛ የእድገት ደረጃ ለመድረስ ያግዛል ተብሎ ይታመናል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በፍጥነት እየተካሄደ ባለበት በአሁኑ ወቅት እየተሰነዘሩ ያሉት ፀረ ልማት ሃሳቦች ተቀባይነት እንደሌላቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም። ግድቡ ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ እየገነባች ካለችው በርካታ ሜጋ የልማት ፕሮጀክቶች አንዱ መሆኑ ይታወቃል።

ከታላቁ የህዳሴው ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው የግድቡ ግንባታ ይፋ ከተደረገበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ባሉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ከወጣው 27 ቢሊዮን ብር ውስጥ 26 ነጥብ 3 በመቶ የሚሆነው ገንዘብ ከኅብረተሰቡ በስጦታ ወይም በቦንድ ግዥ የተሰበሰበ ነው።

ይህ የሚያሳየው የህዝብ አቅምና የሚኮራ ተሳትፎ መኖርን ነው። ይህ ተሳትፎ ግድቡ እስኪጠናቀቅ ድረስ ድጋፉን በተሻለ ሁኔታ አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያጠራጥር ነገር የለውም። በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለግንባታው ትርጉም ያለው የገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑ ደግሞ ሌላው ለስኬቱ አጋዥ ነገር ነው።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በአስተማማኝ የፋይናንስ አቅም ላይ የምትገኝ ከመሆኗም በላይ ለግንባታው በቂ የቴክኒክ አቅም በመፈጠሩ ግድቡ በተያዘለት ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ነው።

በዓባይ ተፋሰስ አጠቃቀምም ሆነ በህዳሴው ግድብ ግንባታ ኢትዮጵያ ያላት አቋም አንድና አንድ ብቻ ነው። በግብጽ ያለው መንግሥት ቀጠለ አልቀጠለ፤ ሌላ መንግሥት ቢመጣም ባይመጣም፤ በግብጽ መረጋጋት ቢፈጠርም ባይፈጠርም ኢትዮጵያ ያላት አቋም የዓባይ ተፋሰስ አገራት የጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀም እንዲኖር ነው። ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀም በቀጠናው ማስፈን ነው። ሁሉም አገራት ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ መፍጠር ነው።

ፊልድ ማርሻል አል ሲሲ ወደ ፕሬዚዳትነት መጡም አልመጡም በዓባይ ተፋሰስ አገራት የውኃ አጠቃቀምና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚኖር ፖለቲካ በግብፅ ምክንያት የሚለወጥ ነገር የለም።

ከታሪክ እንደምንረዳው በአሁኑ ወቅት ግብፅ ውስጥ ያሉት ፖለቲከኞችም ሆነ በቀደሙት ሥርዓታት የነበሩት መንግሥታትና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ያላቸው አቋም ተመሳሳይ ነው። አንድ መንግሥት ተነስቶ ሌላ በመተካቱ ወይም አንድ ግለሰብ ተነስቶ ሌላ በመተካቱ የሚኖር ለውጥ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም።

ስለዚህ አንዱ በመሄዱና ሌላ በመምጣቱ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት የተሳሳተ ነው። ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ መንግሥት ያለው አቋም ማንም ይሀድ ማንም ይምጣ በዓባይ ተፋሰስ ያሉ አገራት በጋራ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን ፍትሃዊ የውኃ ተጠቃሚነት መረጋገጥ እንዳለበት ያሰምርበታል።

የአንዱን አገር ጥቅም አስከብሮ የሌላውን አገር ጥቅም የሚጎዳ ባለመሆኑ በሁሉም የተፋሰሱ አገራት ተቀባይነትን አግኝቷል። ሁሉም የተፋሰሱ አገራት ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የማልማትና የመጠቀም መብት እንዳላትና ይህ መብቷ ማንም የሚሰጣት ማንም የሚነጥቃት እንዳልሆነም በግልጽ መናገር ጀምረዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥትም ቢሆኑ ከዚህ የተለየ አቋም የላቸውም። በራሳቸው ተፈጥሮ ሃብት የመጠቀም መብታቸው የተጠበቀ እንደሆነና ይህንን የመጠቀም መብታቸውን ሲጠቀሙ ደግሞ የቀጠናውን ህዝብ ከተቻለ በሚጠቅም መንገድ ካልሆነ ደግሞ በማይጎዳ ሁኔታ መጠቀም እንዳለባቸው ያምናሉ።

ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብም ከዚህ መነሻ እየተገነባ ያለ ፕሮጀክት መሆኑን ደጋግመው ለማስረዳት ጥረት አድርገዋል። ግድቡ ግብጽንም ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል መሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ብቻ ሳይሆኑ ዓለም አቀፉ የባለሙያዎች ቡድን ሳይቀር አስምሮበታል። ይሁን እንጂ ግብጽ ይህንን እወነታ ለመቀበል አልፈለገችም።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በሚመለከት ኢትዮጵያ ካርቱም ላይ ያደረገችው የመድረክ ውይይት ላይም ይህንን አቋሟን በግልጽ አስታውቃለች። በዋናነት በካርቱም በተካሄደው ሕዝባዊ ዲፕሎማሲ የግብፅ ዜግነት ያላቸው ጭምር ግድቡ ለተፋሰሱ የታችኛው አገራትም ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ ቦንድ ለመግዛት ቃል የገቡ ሱዳናዊያንና ግብጻውያን መኖራቸው ኢትዮጵያ ምን ያህል ፍትሃዊ አቋም መያዟን የሚያረጋግጥ ነው።

የሱዳን መንግሥትና ህዝብ የኢትዮጵያ አቋም ትክክለኛ መሆኑን አምነው ተቀብለዋል። ለጋራ ተጠቃሚነትም ለመሥራት ተስማምተዋል። የግብፅ ህዝብም ቢሆን ኢትዮጵያ የግብጽ ሕዝብ የሚጎዳ ልማት እንደማታካሂድ እምነት አለው።

በርካታ ግብጻዊያን ምሁራን የአገራቸውን ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ እያራመደች ያለው አቋም ትክክለኛ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ጋር ለጋራ ተጠቃሚነት እንዲሰሩ ከመምከር እንዳልተቆጠቡ አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ።

ይሁንና የግብጽ ፖለቲከኞች ዓይናቸውን ጨፍነዋል። በግልጽ የሚታየው ነገር ለእነሱ ጨለማ ሆኖባቸዋል። ጠቀሜታው የራሳቸው ምሁራን ሳይቀር የሚመሰክሩለትን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ለግብጽ ህዝብ አይጠቅምም በማለት ለአገር ውስጥ የፖለቲካ ፍጆታ እያዋሉት ይገኛሉ።

ከዚህ አንጻር አገሪቱ እያደረገች ያለው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴም ድጋፍ ያስገኝላታል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። ከመጀመሪያው ዓይኗን ጨፍና እየገባችበት ያለ በመሆኑ። በርካታ አገራት ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ የተረዱ በመሆኑ። ጥረቱ እንደ ቀደመው ሁሉ ከንቱ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

በግብጽ ውጥረት ነግሷል፤ ህዝቧም ታምሷል። የግብጽ ፖለቲከኞች አገራቸውን ማረጋጋትና ህዝባቸውን ወደተረጋጋ ህይወት መመለስ አልቻሉም። ይልቁንም በአራት ጎራ ተከፋፍለው ህዝቡን ለእልቂት እየዳረጉት ይገኛሉ።

የቅርብ ቀናት መረጃዎች እንደሚያሳዩት የግብጽ ፍርድ ቤት 528 ዜጎች በሞት እንዲቀጡ ወስኗል። በግብጽ ያለው አለመረጋጋትና ውጥረት ማርገቢያ ያጠረባቸው የግብጽ ፖለቲከኞች የህዳሴው ግድብን የፖለቲካ አጀንዳ ማድረግ መምረጣቸው የሚደንቅ አይደለም።

ሆኖም ግን ይህ አማራጭ ለግብጽ አዋጭ እንዳልሆነ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ። እነዚህ በግብጽ የተመሠረቱ ቡድኖች የማይታረቁ ሆነዋል። ግብጽ በዚህ ሁኔታ በሁከትና በውጥረት ተውጣለች። ሕዝቧም ታምሷል። አገሪቱ የህዝቦቿ የግጭት መናኸሪያ ሆናለች። በግብጽ ያለው ሁኔታ ይህንን ከመሰለ ለግብጻዊያኑ ጦርነትን እንደ አማራጭ መጠቀም የሚባለውም የሚያስኬድ እንዳልሆነ መገንዘብ አያዳግትም።

ምናልባት የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለመለወጥና ከውስጥ ይልቅ ወደ ውጭ እንዲመለከት ለማድረግ ፖለቲከኞች ጦርነት የሚለውን ቃል ሊጠቀሙበት ይችሉ ይሆናል።

ሆኖም ግን በኢትዮጵያ ላይ ጦርነትን አውጆ በድል ለማጠናቀቅ የሚያስችል ይቅርና ጦርነት የሚያስጀምር የተመቸ ሁኔታ ባለመኖሩ ግብጽ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ታውጃለች የሚለው ነገር በብዙ ምሁራን ዘንድ ውኃ የማይቋጥር እንደሆነ ይነገራል።

ግብጽ በዲፕሎማሲ መንገድ የህዳሴውን ግድብ ለማደናቀፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች። ላላፉት ሦስት ዓመታት አጠናክራ ሰርታበታለች። ሆኖም ግን መፍትሄ ሊሆናት አልቻለም።

የኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ከተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ላፍታ እንኳን እንዳልተጎተተ ከፕሮጀክቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ይህ የዲፕሎማሲ ጥረት ለግብጽ አማራጭ አይደለም። በዚህ መልክም ግብጽ ህዝቧን መጥቀም አትችልም።

ከላይ እንደተገለፀው ጦርነት የሚባለውም ቢሆን ለግጽ አማራጭ እንዳልሆነ ቀርቧል። ግብጽ ሁለት ብቸኛ አማራጮች አሏት። አንደኛው አማራጭ ከዓባይ ተፋሰሱ አባል አገራት ጋር ተባብሮ መሥራት ነው።

በዚህ ረገድ አገራቱ የፈረሙትን አዲሱ ፍትሃዊ የውኃ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጠውን ሰነድ ላይ መፈረምና በዚሁ ሰነድ መሠረት ከሌሎቹ አገራት ጋር ተጣጥም ሰርታ በጋራ መጠቀም ነው።

በዓባይ ተፋሰስ በሚደረጉ የልማት ፕሮጀክቶች በቀናነት በመሳተፍ የጋራ ተጠቃሚነቷን ማጎልበት ይሆናል። ከዚሁ ተለይቶ የማይታየው ደግሞ ዓለም አቀፉ የባለሙያዎች ቡድን ያቀረበውን ጥናታዊ ሪፖርት በቅንነት ተቀብሎ መተግበር ይሆናል።

ይህ ቡድን በአገራቱ ስምምነት የተቋቋመና ይህንን ሥራ ለመስራት ኃላፊነት ተሰጥቶት በተገቢው መልክ ኃላፊነቱን የተወጣ በመሆኑ ይህንን ውጤት መቀበል ይግድ ይላታል።

ይህንን ውጤት ተቀብላ ከኢትዮጵያና ከሱዳን ጋር በመተባበር መተግበርና የጋራ ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ ይኖርባታል። ታላቁ የህዳሴ ግድብ የግብጽን ህዝብ እንደሚጠቅም ህዝቧን ማሳመንና በጋራ ለመሥራትና ለመበልፀግ መወሰን ይጠበቅባታል።

የቅኝ ግዛት አስተሳሰብና የውኃ ሞኖፖሊ ስምምነቶች ውድቅ መሆናቸውን በመገንዘብ ከዘመኑ ጋር ለመሄድ ራስን ማስተካከል ያሻታል። ይህ ብቻ ነው የግብጽ አማራጭ። ከዚህ የተለየ አማራጭ እንደሌላት የግብጽ ፖለቲከኞች ሊገነዘቡ የግድ ይላል።